ጌታችሁ የሚያፍርና ቸር ነው። ባሪያው የልመና እጆቹን ወደርሱ ከፍ አድርጎ ለምኖት በባዶ መመለስን ያፍራል።

ከሰልማን - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "ጌታችሁ የሚያፍርና ቸር ነው። ባሪያው የልመና እጆቹን ወደርሱ ከፍ አድርጎ ለምኖት በባዶ መመለስን ያፍራል።"»
[ሐሰን ነው።] [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዱዓእ ስናደርግ እጅን ከፍ በማድረግ ላይ አነሳሱ። አላህ (ሐይዩን) እጅግ በጣም የሚያፍር፤ መስጠትን የማይተው፤ ለባሪያው የሚያስደስተውን የሚያደርግና የሚጎዳውን የሚያስቀርለት ነው። (ከሪሙን) ሳይጠየቅ የሚሰጥ ቸር ነው። ከተጠየቀ በኋላስ (እንዴት ሊመልሰው ይሆን)?! አማኝ ባሪያው ለዱዓ ሁለት እጆቹን አንስቶ ለምኖት ለርሱ ባዶ አድርጎ መመለስን ያፍራል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5499